| | Company Name: ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት TOURISM TRAINING INSTITUTE | | Document No.: OF/TTI/PR/007 |
|---|---|---|---|
| Title: የዜና መጽሔት ቅጽ | | Issue No. 1 | Page No.: Page 1 of 1 |

መስከረም/2017

# የ2016 ዓ ም የምረቃት ፕሮግራም

**"በዚህ ወሳኝ ወቅት መመረቃችሁ የዘርፉን የሰው ሀይል ጉድለት ከመሙላት፣ ዘርፉን በማዘመን የአገልግሎት ጥራትን እና የመስተንግዶ ቅልጥፍናን ከማሻሻል ባሻገር የኢትዮጵያ ገጾች ጭምር በመሆናችሁ ኃላፊነታችሁ ከፍ ያለ ነው፡፡"**



ክብርት ወ/ሮ ሙፈሪያት ካሚል
የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር
ቱ.ማ.ኢ. ጳጉሜ 02/2016 ዓ.ም

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በሆቴልና ቱሪዝም ሙያዎች በዲግሪና በደረጃ በተለያዩ መርሐ ግብሮች ያሰለጠናቸውን 478 ሰልጣኞችን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርና ተጠሪው ተቋማት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የሙያ ማህበራት አመራሮች፣ የዘርፉ ባለሀብቶችና ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት በታላቅ ድምቀት አስመርቋል፡፡

በምረቃ መርሐ ግብሩ ላይ ለተመራቂዎች የስራ መመሪያ የሰጡት የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወ/ሮ ሙፈሪያት ካሚል የቱሪዝም ዘርፉ በሀገራችን ኢኮኖሚ ውስጥ ወሳኝ ሚና ካላቸው ዘርፎች መካከል አንዱና ዋነኛው ቢሆንም በሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት ዘርፉ ለረዥም ተግዳሮት ሆኖ መቆየቱን ገልጸው ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ መንግስት በሰጠው ልዩ ትኩረት የቱሪዝም ዘርፉ ከመቼውም ጊዜ በተሻለ እየተነቃቃ ይገኛል ብለዋል፡፡

በዚህ ወሳኝ ወቅት መመረቃችሁ የዘርፉን የሰው ሀይል ጉድለት ከመሙላት፣ ዘርፉን በማዘመን የአገልግሎት ጥራትን እና የመስተንግዶ ቅልጥፍናን ከማሻሻል ባሻገር የኢትዮጵያ ገጾች ጭምር በመሆናችሁ ኃላፊነታችሁ ከፍ ያለ ነው ብለዋል፡፡



የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ በበኩላቸው መንግስት በሆቴልና ቱሪዝም መስክ ብቃት ያለውን የሰው ሀይል በማፍራት የአገራችንን የቱሪዝምና የሆስፒታሊቲ ዘርፉን ለማሳደግ ሁነኛ አቋም በያዘበት ወቅትና እጅግ ተጨባጭ የሆኑ ውጤቶች መታየት በጀመሩበት ወቅት ላይ ስልጠናችሁን በማጠናቀቅ ለመመረቅ በመብቃታችሁ፣ በቀጣይ በዚህ ረገድ የሚጠበቅባችሁን ሙያዊ አስተዋጽዖ ለማበርከት የላቀ ሚና ያላችሁ መሆኑን ተገንዝባችሁ በቆይታችሁ ወቅት በወሰዳችሁት ስልጠና የቀሰማችሁት ዕውቀት፣ ክህሎት እና የተላበሳችሁትን የሙያ ሥነ-ምግባር ተጠቅማችሁ ብሎም የራሳችሁን ጥረት አክላችሁ ሀገርን ለማገልገል ዝግጁ እንድትሆኑ በማለት አሳስበዋል ፡፡

በዕለቱ ከፍተኛ ወጤት ላስመዘገቡ ሰልጣኞች የሜዳልያና የዋንጫ ሽልማት፣ በትብብር አብሮ እየሰሩ ለነበሩ ድርጅቶችም የእውቅና ምስክር ወረቀት እንዲሁም የማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ የተግባር ስልጠና በመስጠት የራሳቸውን የሥራ ዕድል መፍጠር ለቻሉ ሴት ሰራተኞች እውቅና ተሰጥቷል፡፡








በኮምኒኬሽን ጉዳዮች ስራ አስፈጻሚ ክፍል የተዘጋጀ

| | Company Name: ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት TOURISM TRAINING INSTITUTE | Document No.: OF/TTI/PR/0o7 | |
|---|---|---|---|
| Title: የዜና መጽሔት ቅጽ | | Issue No. 1 | Page No.: Page 1 of 1 |

**ኢንስቲትዩቱ ከአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በ2017 በጀት ዓመት በቅንጅት ለመስራት ተፈራረመ፡፡**



ቱ.ማ.ኢ. ነሐሴ 23/2016 ዓ.ም

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በ2017 በጀት ዓመት በቅንጅታዊ አሰራር፣ ትብብርና ትስስር አብሮ ለመስራት የኢንስቲትዩቱ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ክብረት እና የቢሮው ኃላፊ ሂሩት ካሳው(ዶ/ር) ተፈራረሙ፡፡
የጋራ ፊርማ ሥነ ሥርዓቱ በዓመቱ እስከ 2000 ለሚደርሱ የሆቴልና ቱሪዝም ሙያተኞች የሥራ ላይ ስልጠና ለመስጠት መሆኑን የገለጹት የኢንስቲትዩቱ የስልጠናና አቅም ግምባታ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ክብረት ይህ የከተማውን የቱሪዝም አገልግሎት ለማሻሻል እጅግ ጠቃሚ ነው ብለዋል፡፡
በከተማው እየተሰራ ካለው የቱሪዝም መሰረተ ልማት አንጻር የተሻለ አገልግሎት መስጠት ለሀገር ገጽታ ግንባታ መሠረት በመሆኑ ማሰልጠኛ ኢንስቲትቱ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት እንደሚጠቅም አቶ ሀብታሙ ክብረት ገልጸዋል፡፡
የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሳው (ዶ/ር) በበኩላቸው በ2017 በጀት ዓመት ያቀድናቸውን ስራዎች ይበልጥ በተጠናከረ መልኩ ተንቀሳቅሰን በተሻለ ትብብርና ቅንጅት በመስራት አመርቂ ውጤት እናመጣለን ብለዋል።

"**ለውጥ የሚጀምረው ንቁ ከመሆን ነው**"

ቱ.ማ.ኢ .
ነሃሴ 22/2016 ዓ ም




ለቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሴት ሰራተኞች ይሰጥ የነበረው የትራንስፎርሜሽናል አመራርነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ።
በዚህ ስልጠና ማጠቃለያ የተገኙት የተቋሙ ሥራ አመራርና አስተዳደር ዘርፍ ም/ ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ እንደገለጹት ሴቶች በተቋሙ ባሉት ሥራዎች ሁሉ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸውና እነሱን ማሰልጠን የተቋሙን ማህበረሰብ ማሰልጠን እንደሆነ ተናግረዋል።



ስልጠናውን የሰጡት አሰልጣኞች ከሲቪል ሰርቪስ ወ/ሮ ሰርገወርቅ ሲሳይና ወ/ሮ ምንዳዬ ዮሐንስ ሲሆኑ በዛሬው እለት ሰሜታችንን እንዴት መቆጣጠር ፣ ራስን በማወቅ እና በመግዛት ማህበረሰብን ማወቅ እንደሚቻል፤ እንዲሁም የግንኙነት አስተዳደር በማስፋት ጥሩ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ስልጠና ሰጥተዋል ።
ወ/ሮ ሰርገወርቅ ለውጥ የሚጀምረው ንቁ ከመሆንና የራሰን ሰሜትና የሰዎችን በመለየት በአስፈላጊው ቦታና ጊዜ ስንጠቀም እንደሆነ ገልጸዋል።



የተቋሙ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሥራ አስፈጻሚ ወ/ሮ ንግስት ሲሳይ አሰልጣኞች ሰልጠናውን በትኩረት ስለተከታተሉ አመስግነው ስልጠናውን ወደተግባር መለወጥ እንዳለባቸውም አሳስበዋል፡፡ስልጠናውን የወሰዱት ሴቶችም ስልጠናው ወቅቱን የጠበቀ መሆኑን በመግለፅ ለሴቶች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የተቋሙ ማህበረሰብ የሚያስፈልግ መሆኑን በመጠቆም ስልጠናውን ያዘጋጁትንን የEASTRP ፕሮጀክት አስተባባሪዎችና የተቋሙ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች አካቶ ክፍልን አመስግነዋል።





በኮምኒኬሽን ጉዳዮች ስራ አስፈጻሚ ክፍል የተዘጋጀ

| Company Name: | Document No.: |
|---|---|
| ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት<br>TOURISM TRAINING INSTITUTE | OF/TTI/PR/007 |

| Title | Issue No. | Page No.: |
|---|---|---|
| የዜና መጽሔት ቅጽ | 1 | Page 1 of 1 |

**ኢንስቲትዩቱ በተለያዩ ክልሎች እና ዞኖች ያጠናቸውን ባህላዊ ምግቦች በምግብ ዝርዝር ውስጥ ለማካተት እና ለገበያ ለማቅረብ እንዲቻል ከሀይሌ ግራንድ ሆቴል ጋር የሰነድ ርክብክብ አካሄደ**



ቱ .ማ. ኢ. ነሐሴ 3/2016 ዓ ም

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የሲዳማ፣ የአፋር እና የሀረሪ፣ የጋምቤላ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ ባህላዊ ምግቦችን በማጥናት በባለ ኮከብ ሆቴሎች በምግብ ዝርዝር እንዲገቡ በማድረግ ወደ ሀገራችን የሚመጡ የውጭ ጎብኝዎችም ሆኑ በሀገራችን ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩ ዜጎች ባህላዊ ምግቦችን በፈለጉት አካባቢ እንዲያገኙ የሚያስችል መሆኑን የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ም/ ዋና ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ስዩም ገልጸዋል።

እንዚህን ምግቦች በባለኮከብ ሆቴሎች በምግብ ዝርዝር ከማካተት ባሻገር ለሥራ እድል ፈጠራ እና ዘርፈ ብዙ ለሆነ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጥቅም ማዋል እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በዚህ ሰነድ ርክብክብ ወቅት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት የሰነድ ዝግጅቱ በየክልሎቹ የሚገኙ የብሄሩ ተወላጅ እናቶች ጋር በመሄድ በተቋሙ ባለሙያዎች ተደግፎ የተሰራ ሲሆን፣ ሥራው ሲሰራ ከአንዱ ክልል፤ ወደ ሌላ ክልል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ እና እሴት እየተጨመረበት መምጣቱን በመጠቀም በቀጣይም የባለድርሻ አካላትን አስተያየት በማካታት በሌሎች ክልሎችም ጥናቱ የሚካሄድ መሆኑን አሳውቀዋል።

የሀይሌ ግራንድ ሆቴል ዋና ስራአስኪያጅ አቶ እምሻው ተሾመ በበኩላቸው ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ለሀገራችን ባህል ትኩረት ተሰጥቶ ይህንን ሰነድ በማዘጋጀት ማቅረቡ የሚያስመሰግን መሆኑን ጠቅሰው የሀይሌ ግራንድ ሆቴል በአዲስ መልክ ባህላዊ ይዘት ያላቸውን ምግቦች ለማዘጋጀት በዝግጅት ላይ ባለንበት ወቅት ቀድሞ ተቋሙ በመምጣቱ ደስተኛ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ዋና ሥራ አስኪያጁ እነዚህ የተለያዩ አከባቢ ባህላዊ ምግቦች በምግብ ዝርዝር ውስጥ ለማስገባት እንደተግዳሮት የሚነሳውን የግብዓት እጥረትና የክህሎት ክፍተቶች በተባለው ልክ ከተሟላ በሆቴላችን የበርካታ ክልል ምግቦች በምግብ ዝርዝራችን በማካተት ቀዳሚ እንደሚሆኑ ተናግረዋል።



አቶ ይታሰብም እነዚህን ባህላዊ የምግብ አይነቶችን ለማዘጋጀት ተግዳሮት የሚሆኑ የግብዓት ችግሮችን ከክልሎች ጋር ትስስር በመፍጠር ማሻሻል እንደሚቻልና የክህሎት ክፍተቶችን በማሰልጠኛው አሰልጣኞች ድጋፍ ማግኘት እንደሚችሉ ገልጸዋል።

የሆቴሉ የኦፐሬሽን ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ እጅጉ እንዳሻው በበኩላቸዉ ማሰልጠኛ ተቋሙ እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ አድንቀው ሰነዱን ተቀብለው ሥራ ላይ ለማዋል ቁርጠኛ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡

ከዚህ ቀደም የመጀመሪያው ባህላዊ የምግብ ዝግጅት አሰራር ሰነድ እና ስምምነት በካፒታል ሆቴል መካሄዱንና በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ደግሞ በገነት ሆቴል በምግብ ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ ምግቦች ቅምሻ ተደርጓል ፡፡



**በገነት ሆቴል ለቅምሻ ከቀረቡት በከፊል**

**"የምትተክል ሀገር የሚያጸና ትውልድ "**

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በቦሌ ለሚክፍለ ከተማ እና በሸገር ከተማ አስተዳደር መነ አብቹ ክ/ከተማ  ችግኝ ተከሉ።

ቱ.ማ.ኢ. ሐምሌ 25/2016 ዓ.ም

"የምትተክል ሀገር የሚያጸና ትውልድ " በሚል ሀገራዊ መሪ ቃል ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በቦሌ ለሚ እንዱስትሪ ፓርክ ችግኝ ተከሉ።

የችግኝ ተከላ መርሃ ግብሩን ያስጀመሩት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ ዛሬ የምንተክለው ችግኝ ነገ ለልጆቻችን የተሻለች ሀገርን ለማስረከብ፣ ለዜጎች የሥራ እድልንም ለመፍጠር የሚያግዝ ነው ብለዋል።

ከዚህ በፊት ተቋሙ በጥያ ትክል ድንጋይ፣ ፖርቹጋል ድልድይ እና ሌሎችም ቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች ላይ የተተከሉ 80 በመቶ ችግኞች መጽደቃቸውን የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ ከዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ከቢሮ ጋር የሀገራችንን ቱሪዝም ለማሳደግ ለአንድ ዓላማ አብረን እየሰራን እንገኛለን ብለዋል።

የቢሮው ም/ኃላፊ አቶ ሀፍቶም ገ/ እግዚአብሔር በበኩላቸው ኢንስቲትዩቱ በቱሪዝም ዘርፍ እያበረከተ ካለው አስተዋጽኦ በተጨማሪ በመዳረሻዎች አካባቢ እያደረገ ያለው የችግኝ ተከላ መርሐግብር የሚበረታታ እንደሆነ ገልጸው ዛሬ አብረን የተከልነውን በጋራ ተንከባክበን እናለማለን ብለዋል።



በዚህ መርሐ ግብር 2000 ችግኞች የተተከሉ ሲሆን በኢንስቲትዩቱ በክረምት እየሰለጠኑ ያሉ የሸጋ ትውልድ ህፃናትም ተሳትፈዋል።

ሁለተኛ ዙር ችግኝ ተከላ መርሃ ግብር የኢንስቲትዩቱ ማህበረሰብ በሸገር ከተማ አስተዳደር መነ አብቹ ክ/ከተማ አከናወኑ።



የችግኝ ተከላ መርሃ ግብሩ ላይ የተገኙት የማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ ቱሪዝምና አረንጓዴ አሻራ የሚለያዩ አይደለም፣ መነ አብቹ ክፍለ ከተማ ተገኝተን ዛሬ ብቻ ችግኝ ተክለን የምንሄድ ሳይሆን በቀጣይ ኢንስቲትዩቱ በሚያከናውናቸው የስልጠና እና ምርምር ስራዎች በጋራ እንሰራለን ብለዋል።



የመነ አብቹ ክፍለ ከተማ አስተዳዳሪ አቶ አብርሃም ብርሃኑ ኢንስቲትዩቱ በሰሜን በር መውጫ በሆነው አካባቢ ችግኝ ለመትከል ስለመረጠ እናመሰግናለን ፣ ዛሬ የሚተከሉ ችግኞች እንዲጸድቁ እና በሌሎችም ጉዳዮች አብረን እንሰራለን ብለዋል።

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሰራተኞችና ማኔጅመንት አባላት ሁለተኛ ዙር በመነ አብቹ ክ/ከተማ ሱሉልታ አካባቢ ኢፋ ቦሩ መልካ ሀዩ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተተከሉት ችግኞች 1500 ሲሆኑ ለምግብነት፣ ለደንና ውበት የሚያገለግሉ መሆናቸው ተገልጿል፡፡

የችግኝ ተከላ መርሃ ግብሩ ላይ የተገኙት የማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ ቱሪዝምና አረንጓዴ አሻራ የሚለያዩ አይደለም፣ መነ አብቹ ክፍለ ከተማ ተገኝተን ዛሬ ብቻ ችግኝ ተክለን የምንሄድ ሳይሆን በቀጣይ ኢንስቲትዩቱ በሚያከናውናቸው የስልጠና እና ምርምር ስራዎች በጋራ እንሰራለን ብለዋል።

የመነ አብቹ ክፍለ ከተማ አስተዳዳሪ አቶ አብርሃም ብርሃኑ ኢንስቲትዩቱ በሰሜን በር መውጫ በሆነው አካባቢ ችግኝ ለመትከል ስለመረጠ እናመሰግናለን ፣ ዛሬ የሚተከሉ ችግኞች እንዲጸድቁ እና በሌሎችም ጉዳዮች አብረን እንሰራለን ብለዋል።

## በትግራይ ክልል የሚገኘውን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ለማሳደግ እንዲቻል በስልጠና፣ ምርምርና ማማከር በሚሰሩ ስራዎች ዙሪያ ውይይት ተካሄደ።

ቱ.ማ.ኢ. ሐምሌ 26/2016 ዓ.ም

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከትግራይ ክልል ቱሪዝም ባለድርሻዎች ጋር በመሆን በክልሉ የሚገኘውን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ለማሳደግ አብሮ መስራት በሚቻልባቸው አጀንዳዎች ላይ ውይይት ተደርጓል።



በኢንስቲትዩቱ በኩል ከክልሉ ጋር መስራት የሚቻልባቸውን ዘርፎች ማብራሪያ የሰጡት አቶ ታደሰ ሞላ ኢንስቲትዩቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሆቴልና ቱሪዝም ሙያዎች ብቃት ያለውን የሰው ሀይል ለማፍራት ፣ ችግር ፈቺ ምርምሮችን በማካሄድ እንዲሁም በምክር አገልግሎት እያደረገ ያለውን ማብራሪያ ሰጥቷል። ቱሪስቶችን ለመሳብ ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት ከመንግስት ቢሮዎች ጀምሮ ለሁሉም ቱሪዝም ባለድርሻዎች ስልጠናዎችን መስጠት በዘርፉ እየሰሩ ያሉ አካላትን የሚያነቃቃ መሆኑን የገለጹት በኢንስቲትዩቱ የአጫጭርና ተከታታይ ት/ት ክፍል ኃላፊ አቶ ግርማ ደቀባ በዘርፉ እየተተገበረ በሚገኘው ፖሊሲና ስትራቴጅዎችም ጭምር ስልጠና መስጠት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

የትግራይ ክልል የቴክኒክና ሙያ ስልጠና እና የስራና ክህሎት ም/ቢሮ ኃላፊ አቶ አለም አረጋዊ የክልሉን ቱሪዝም ለማጠናከር ከኢንስቲትዩቱ ጋር በመሆን በአጭር፣ በመካከለኛና ረጅም ጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ስራዎችን ዕቅድ በማዘጋጀት በተለይ በግበያ ትስስር ፣ ለዘርፉ ተዋናዮች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች እና የስልጠና ተቋማትን ለማደራጀት የግብዓት ድጋፎች የሚደረጉበት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይገባል ብለዋል።

የሀገር በቀል ግብረ ሰናይ ድርጅት የወጣቶች ዘሊቂ ተጠቃሚነት ድርጅት (TYES) ኃላፊ አቶ ዳዊት ኃይሉ በበኩላቸው የተጀመረው ውይይት የስራ እድልን ለመፍጠር በተለይም የወጣቶችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚረዳ በመሆኑ አስፈላጊውን በቅርበት የማስተባበር ስራውን እንደሚያከናውኑ ገልጸዋል ።

በውይይቱ ላይ የኢንስቲትዩቱ ተወካዮች፣ የክልሉ ቴክኒክና ሙያ እና ሥራና ክህሎት ቢሮ ፣ የአስጎብኝ ድርጅቶች ማህበር ፣ የመቀሌ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ፣የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ የክልሉ ሆቴሎች ማህበር እና ሀገር በቀል ግብረ ሰናይ ድርጅት የወጣቶች ዘሊቂ ተጠቃሚነት ድርጅት (TYES) ተሳትፈዋል።

| | Company Name: | Document No.: |
|---|---|---|
| | **ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት** TOURISM TRAINING INSTITUTE | OF/TTI/PR/007 |
| Title: **የዜና መጽሔት ቅጽ** | Issue No. 1 | Page No.: Page 1 of 1 |



**ማስልጠኛ ኢንስቲትዩቱና የኦስትሪያ አምባሲ አብሮ ለመስራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አካሄዱ።**

ቱ.ማ.ኢ ሐምሌ 12 / 2016 ዓ.ም

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትና የኦስትሪያ አምባሲ በቱሪዝም ዘርፍ አብሮ ለመስራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎችና አምባሳደር ሲሞኔ ናፕ ውይይት አካሂዷል።

ሀገራችን ከፍተኛ የቱሪዝም ሀብት ያላት በመሆኑ የማሰልጠኛ ተቋሙ ለዘርፉ የሚሆን የሰለጠነ የሰው ሀይል በማቅረብ፣ የተለያዩ ጥናትና ምርምሮች እንደሁም የማማከር አገልገሎትን እየሰጠ እንደሚገኝ ማብራሪያ የሰጡት የኢንስቲትዩቱ የምርምርና ማማከር ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ስዩም በአቅም ግንባታ፣ ኢንዱስትሪው ተለዋዋጭ ባህሪ አንጻር በልምድ ልውውጥ እና በመሰረተ ልማት ዘርፍ በዘላቂነት ከአንባሲው ጋር ለመስራት ፍላጎት እንዳለ ገልጸዋል፡፡



መንግስት ለቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን የገለጹት የኢንስቲትዩቱ አስተዳደርና ሥራ አመራርና ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ከኢምባሲው እና እንደ ሀገርም የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ በዘላቂነት በትብብር አብሮ መስራት ይቻላል ብለዋል፡፡

የኦስትሪያ አምባሳደር ሲሞኔ ናፕ በበኩላቸው ሀገራቸው ከአውሮፓ ሀገሮች በቱሪዝም ገቢ ሁለተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ መሆኗን ገልጸው የኢትዮጵያ መንግስት ለቱሪዝም ዘርፍ የሰጠውን ትኩረት አድንቀዋል፡፡ ቱሪዝም እንደ ሀገርም ሆነ በቀጠናው በጣም አስፈላጊ የኢኮኖሚ መስክ ሆኖ እንዲቀጥል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብለዋል፡፡ ኢምባሲው ከተለያዩ የሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር እየሰራ እንደሚገኝ የገለጹት አምባሳደር ሲሞን ናፕ ከቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ጋር በቀጣይነት በትብብር እንደሚሰራ ገልጸዋል።




"

## ሀገር በቀል እውቀቶቻችንን ካጠናከርን የሌለን ነገር የለም” አቶ ገዛኸኝ አባተ

ቱ.ማ.ኢ ሐምሌ 08/ 2016 ዓ.ም

ሀገር በቀል የበጎ አድራጎት ድርጅት የሆነው ሸጋ ትውልድ ማህበርና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በጋራ በመሆን ለአንድ ወር የሚቆይ የታዳጊዎች የሕይወት ክህሎት ስልጠና መስጠት ጀመሩ።



በስልጠና ማስጀመሪያ መርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት የቱሪዝም ማሰልኛ ኢንስቲትዩት ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ስልጠናው የሀገር በቀል እውቀቶችንም የሚያካትት በመሆኑ ሀገር በቀል እውቀቶቻችንን ካጠናከርን የሌለን ነገር የለም ብለዋል።

ወቅቱ የሚፈልገው ክህሎት ጋር ለመድረስ የህይወት ክህሎት አስፈላጊ ነው ያሉት አቶ ገዛኸኝ አባተ ታዳጊዎች ሀገር በቀል እውቀትን ከቴክኖሎጂ ጋር በማስተሳሰር ሀገርን ማሳደግ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡

የሸጋ ትውልድ ማህበር ሰብሳቢ አቶ ሳሙኤል ገረመው ማህበሩ ለሀገር እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉ ታዳጊዎችን ከቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ስልጠና እየሰጠ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ ላለፉት ሁለት ዓመታት የነበሩ የስልጠናዎችን ብዙ ተሰጥኦ ያላቸው ታዳጊዎችን ለሀገር ማበርከት እንደተቻለም ገልጸዋል፡፡ በዚህ የክረምት ወቅት ለአንድ ወር የሚቆይ ሀገር በቀል እውቀቶችና ቴክኖሎጂ ላይ ያተኮተሩ ታዳጊዎች ተሰጥዎአቸውን ሊያውቁበት የሚችሉበት ስልጠናዎች እንደሚሰጡ አቶ ሳሙኤል ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በስልጠና ማስጀመሪያ መርሐ ግብሩ ላይ የበጎ አድራጎቱ ድርጅት አመራሮችና ቦርድ አባላት እንዲሁም ከዚህ በፊት በተሰጡ የህይወት ክህሎት ስልጠና በመውሰድ የተሻለ ሥራ እየሰሩ የሚገኙ ታዳጊዎች ተገኝተዋል፡፡



## ኢንስቲትዩቱ የክህሎት ስልጠና ለሰጣቸው ወጣቶች ሥራ መጀመር የሚያስችል ተንቀሳቃሽ የምግብ ማብሰያ ማሽን አበረከተ።

**ቱ.ማ.ኢ ሐምሌ 05/2016 ዓ.ም**



ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 11 ለሚገኙ ከዚህ በፊት የክህሎት ስልጠና ለሰጣቸው ወጣቶች ሥራ መጀመር የሚያስችል ተንቀሳቃሽ ምግብ ማብሰያ ሶስት ማሽን ለወረዳው ስራ አስፈጻሚ አስረከበ፡፡

በርክክቡ ላይ የተገኙት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ ለወጣቶቹ የተዘጋጀው ማሽን ከተቋሙ ተልዕኮ በመነሳት የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ለመስጠት መሆኑን ጠቅሰው የስልጠና ተቋማት ሰልጣኞቻቸው የደረሱበትን የመከታተል ኃላፊነት በተቋማቱ ላይ የተጣለ ነው ብለዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ከዚህ በፊት ሲያደርግ እንደነበረው በአካባቢው ከሚገኙ ተቋማት ጋር በመተባበር ለወጣቶቹ የሰጠውን የክህሎት ስልጠና ወደ ተግባር የሚቀይሩበት እንደሆነና የተጀመረው ድጋፍም ቀጣይነት እንዳለው አቶ ጌታቸው ነጋሽ ገልጸዋል፡፡

በዚህ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ወጣቶቹ ተከታታይነት ያለውን ድጋፍ በማግኘት ወደ ኢንተርፕራይዝ እንዲያድጉ ይደረጋል ብለዋል፡፡

የተዘጋጀው ማሽን ከሁለት መቶ ሺህ ብር በላይ ወጪ የተደረገበት በሶስት ቡድን ሊሰራበት የሚችል፣ በራሳችን ዲዛይን የተጋጀ ነው ያሉት የኢንስቲትዩቱ ጥናትና ምርምር እና ማማከር ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ስዩም ወረዳው ባለው አደረጃጀት ለወጣቶቹ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና በመረጡት የሙያ መስክ የክህሎት ስልጠና ተሰጥቷቸዋል ብለዋል። እንደዚህ አይነት ማሽኖች በተለይ አሁን እየተሰራ ከሚገኘው የኮሊደር ልማት ጋር ተያይዞ እየተዘጋጀ በሚገኘው የእግረኛ መንገድ ላይ እንደ አማራጭ የምግብ ማቅረብ እንደሚችልም ም/ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል ።



የወረዳ 11 ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ደህንነት ገብሩ በበኩላቸው ለወጣቶቹ የመስሪያ ቦታ የተዘጋጀላቸው መሆኑን ገልፀው ከኢንስቲትዩቱ ጋር በተፈራረሙት የመግባቢያ ሰነድ መሰረት ተገቢውን ድጋፍና ክትትል እንደሚደረግ ገልፀዋል። ኢንስቲትዩቱ እያደረገ ላለው ድጋፍ እናመሰግናለን ብለዋል።

አንዱ ማሽን ላይ እስከ ሶስት ሰዎች መስራት እንደሚችሉ ተገልጿል።

ከምረቃት ፎቶ በከፍል













የሴቶች ስልጠና ፎቶ በከፍል



